

Australian Government
Organ and Tissue Authority

# ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን በእርዳታ መስጠት እንዴት መወያየት እንዳለበት።

አንድ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን በመርዳት እስከ 10 የሰዎች ህይወትን ማትረፍ ይቻላል።

ለሰውነት ክፍልና ለህዋሳት ቡድን በእርዳታ ለማቅረብ ወስነው ከሆነ ታዲያ ከቤተሰብዎ ጋር መወያየቱ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በአውስትራሊያ ውስጥ የእያንዳንዱ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን አቅራቢ ለሆነ ቤተሰብ በተወያዩበት ውሳኔ መሰረት እርዳታውን ለማካሄድ ስለሚጠየቁ ነው። በእያንዳንዱ እርዳታ አቅርቦት ውሳኔዎች ላይ የሚያውቁ ቤተሰቦች ለእነዚህ ውሳኔዎች በበለጠ ድጋፍ ይሰጣሉ።

ይህ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም፤ አብዛኛው አውስትራሊያውያን እርዳታ ለመስጠት ፍላጎት ስላላቸውና ጥቂቶቹም ይህንን ለማካሄድ እድሉን ስለሚያገኙ ነው። ከመቶ 1% እጅ የሚሆኑት ሰዎች ብቻ በሆስፒታል ውስጥ የሚሞቱ የሰውነት ክፍልን ለመርዳት በሚያስችል የተወሰኑ ሁኔታዎች እንደሆነና 1,500 የሚሆኑ ሰዎች በማንኛውም ጊዜ ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን በእርዳታ ስለመስጠት አርእስት ከርስዎ ቤተሰብ ጋር ማንሳት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ወይም ስለዚህ ጉዳይ ለመነጋገር ጊዜ ማግኘትር አስቸጋሪ ሆኖ ሊሰማዎት ይችል ይሆናል። ንግግሩን ለመጀመር አንዳንድ ቀለል ያሉ ተግባራዊ ምክሮች በዚህ ጽሁፋዊ ወረቀት ላይ ይቀርብልዎታል።

እንዲሁም ለርስዎ ቤተሰብና ጓደኞች ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ ውይይት (እና ማስታወስ) እንዲችሉ ሊረዳቸው ይችላል።

መጀመሪያ፡ ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ ያለን ተጨባጭ ነገር ማወቅ ነው። በርስዎ ቋንቋ ያካተተ መገልገያ ማግኘት ይችላሉ ወይም በሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ ስለርስዎ የሃይማኖት አቋም መረጃ በድረገጽ www.donatelife.gov.au ላይ ያቀርባል።

ስለዚህ ይህንን ውይይት ለማካሄድ መቼ ነው ጥሩ ጊዜ እንደሆነና እንዴት ይጀምሩታል?

## የቤተሰብ ውይይት ለመጀመር መቼ ነው ጥሩ ጊዜ?

ዛሬ። ስለ ጠቃሚ የሆነ የህይወት ጉዳዮች ማለት ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ ውይይት ለመጀመር በየቀኑ ያሉትን ሁኔታዎች ለውይይት መጠቀም ይችላሉ። በነዚህ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉት:

- የርስዎ ቤተሰብ በሚቀጥለው የምግብ ጊዜ ተሰባስበው ሲቀመጡ
- የህይወት ዋስትና ወይም በጽሁፍ ኑዛዜ በሚደረግበት ጊዜ
- ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤት ሲወጡ
- የቤተሰብ መታሰቢያ ዓመታዊ በአል ሲከበር ወይም በሌላ ልዩ የሆነ ሁኔታ ላይ
- በርስዎ የቤተሰብ ሀኪም/GP ምርመራ ሲካሄድ
- ስለ እርዳታ የሰጠ የሆነ ሰው ሲሰሙ፤ ለማስገባት የፈለገ ወይም ያስገባ የሆነ ሰው ሲሰማ።

ስለ እያንዳንዱ የእርዳታ ውሳኔዎች ከርስዎ ቤተሰብ ጋር ከተወያዩ በኋላ ታዲያ የርስዎን ውሳኔ በመድገም እንደሚያስታውሱ ለማረጋገጥ እነዚህ ሁኔታዎች ጥሩ እድል ሊከፍቱ ይችላሉ።

## ለአንዳንድ ንግግር ጀማሪዎች

ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ ለመወያየት ማበረታታት ለአንዳንድ ሰዎች አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ስለ ሞት ጉዳይ ማንሳቱ ላይመችና አስቸጋሪ ወይም የተከለከለም ሊሆን ይችላል፤ በተለይ ታዳጊ ወጣቶች በሚሳተፉበት ቦታ ላይ።

ውይይቱን ለማበረታታት እንዲረዳ፤ የሚከተሉት የንግግር ጀማሪዎች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ:

- ጓደኛየ ለሰውነት ክፍልና ለህዋሳት ቡድን እርዳታ ለመስጠት እንደተመዘገበ ሰምቻለሁ እንዲሁም እኔም ለመመዝገብ እያሰብኩ ነው። ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ አቅርቦት የርስዎ ሀሳብ ምንድ ነው?
- ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ ጥራዝ ወረቀት አሁን ማየቴ ነው። አንድ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን ሰጪ እስከ 10 የሰው ህይወት እንደሚያተርፍ ያውቃሉን? የመመዝገቢያ ቅጹ ይኸው አለኝ እናም እኔው እራሴ ለጋሽ ለመሆን እያሰብኩኝ ነው።
- ይህንን አስከፊ አደጋ በጋዜጣ ላይ አይቸዋለሁ እናም የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን በእርዳታ ስለመስጠት እንዳስብ አድርጎኛል። አውስትራሊያ በበለጠ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን በእርዳታ አቅራቢዎች በትክክል እንደሚያስፈልጋት አንዳንድ ጥናቶች አካሂጃለሁ፤ ታዲያ አንድ የሰውነት አካል ለጋሽ ከ10 ሰዎች በላይ ህይወትን ያተርፋል።
- ከመቶ 1% እጅ የሚሆኑት ሰዎች ብቻ በሆስፒታል ውስጥ የሚሞቱ የሰውነት ክፍልን ለመርዳት በሚያስችል የተወሰኑ ሁኔታዎች እንደሆነና ይህም ብዙ በበለጠ የሰውነት ህዋሳት ቡድን እርዳታ አቅርቦት እድል ስለሚኖር ነው። የሰውነት ክፍል እርዳታ ሊካሄድ የሚችለው ሆስፒታል ውስጥ በጥልቀት እንክብካቤ ለሚደረግለት ወይም በአደጋና በድንገተኛ ችግር ክፍል በጣም ለየት ባለ ሁኔታዎች ላይ ላሉት ብቻ ይሆናል። ስለዚህ በበለጠ ለማጣራት እንደማስብበትና ለጋሽ ለመሆን እመዘገባለሁ።
- በዚህ የማህበረሰብ ክብረ በዓል ስለ ህይወት ግንዛቤ እና አካል አሰጣጥ ጊዜ በሚናገሩበት ጊዜ እኔ ነበርኩ። እንደሚመስለኝ ስለ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን አቅራቢ ለመሆንና ውሳኔ ለማካሄድ ግምት ውስጥ አስገብቸ አይቸዋለሁ። ይህንን ማድረጉ ጥሩ ነገር ይመስላል።
- በአብዛኛው ሁሉም ሃይማኖቶች ለሰውነት ክፍልና ለህዋሳት ቡድን በእርዳታ መስጠት ላይ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ያውቃሉን? የእኛም ሃይማኖት ከሰውነት ክፍልና ህዋሳት ቡድን እርዳታ ጋር በተዛመደ ደህና ይመስላል። በአሁ ጊዜ ይህ ተቀባይነት እንዳለው አውቃለሁ ታዲያ በአውስትራሊያ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን ለጋሽ ላይ ልመዘገብ ነው። ይህን ነገር ማድረጉ ጥሩ ይመስለኛል ታዲያ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን ለጋሽ በመሆን ህይወትን ማትረፍ እችል ይሆናል።

## ያውቃሉን?

ለጋሽ ለመሆን ውሳኔ በግላዊነት የሚካሄድና ጠቃሚም እንደሆነ ነው። በራስዎ ትክክለኛ ውሳኔ ለማካሄደ፤ እውነታዎችን ማግኘት እንደሚያስፈልግዎ፤ ስለዚህ የርስዎ ውሳኔ ይታወቃል። እንዲሁም የርስዎ ቤተሰብ እውነታዎችን ፈልጎ ለማግኘትና የራሳቸውን ውሳኔዎች ለማካሄድ ጊዜ ሊያስፈልግ ይችላል።

**ፈልጎ ማግኘት** □□ የሰውነት ክፍልና የህዋሳት ቡድን እርዳታ እውነታዎች

**መወሰን** ለጋሽ ስለመሆን እና የርስዎን ውሳኔ በአውስትራሊያ የሰውነት ክፍል ለጋሽ ምዝገባ ላይ ማስመዝገብ

**መወያየት** ከርስዎ ጋር ቅርበት ካለው ሰው ጋር ያለዎትን ውሳኔ ማነጋገር።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወይም ያለዎትን ውሳኔ በአውስትራሊያ የሰውነት ክፍል ለጋሽ ላይ ለማስመዝገብ በድረገጽ ስwww.donatelife.gov.au **ላይ** ይመልከቱ።

The Migrant Centre Organisation Inc.

**Make a positive difference – say YES!**